ሰመጉ
HRCO
የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ
HUMAN RIGHTS COUNCIL

ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው፡፡
HRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.

**ለ ሲዳማ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ**
**ለ ሀዋሳ ከተማ ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ**
**ለሲዳማ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ፓርቲ (ሲብዴን)**

**የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) 146ኛ ልዩ መግለጫን ተከትሎ በተቋሞቻችሁ በኩል ለቀረቡት ቅሬታዎች የተሰጠ ምላሽ**

ጥር 24 ቀን 2011 ዓ.ም

ድርጅታችን የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) የቀድሞዉ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማህበር ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 ዳግም ተመዝግቦ በሕጋዊነት በመንቀሣቀስ ላይ ያለ መንግስታዊ ያልሆነ የሰብአዊ መብቶች ተሚጋች ተቋም ነዉ። ኢሰመጉ (ሰመጉ) ከተመሰረተበት ከመስከረም 1984 ዓ.ም ጀምሮ ባለፉት 27 ዓመታት ስለሙብት መናገር ከፍተኛ ዋጋ በሚያስከፈልበት ጊዜ ሁሉ መንግስት የዜጎችን መብት የማክበር፤የማስከበር እና የማሟላት ግዴታዉን እንዲወጣ፤ሕዝብም መብቱን እንዲያውቅና እንዲያስከብር አበክሮ ሲወተውት፤የሰብአዊ መብቶችን አያያዝ ሲከታተል፤ የመብት ጥሰቶችን በመመርመር ሲያጋልጥ፤ ጥሰት ፈፃሚዎች ተጠያቂ እንዲሆኑ ሲሞግትና የጥሰት ሰለባዎችም ፍትህና ተገቢውን ካሳ እንዲያገኙ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል። ለዚህም ድርጅቱ እስካሁን ያወጣቸዉ 146 የሰብአዊ መብት ጥሰት ምርመራ ዉጤቶች፤ 36 መደበኛ የሰብአዊ መብቶች ሪፖርቶች፤ እጅግ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብት የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮች፤ የእስረኞች አያያዝ ምርመራ ዉጤቶችና የሕግ ምክር አገልግሎቶች አስረጂዎች ናቸዉ። ከሁሉም በላይ በሀገራችን እየተፈፀሙ ያሉት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ብሔርን፣ ፆታን እና ሀይማኖትን የማይለዩ የመሆናቸውን ያህል፤ ሰመጉም ያለ አንዳንች ልዩነት በዜጐቻችን ላይ የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በማጣራት ይፋ ያደርጋል። የአቅም ጉዳይ ካልገደበዉ በቀር በሁሉም የአገሪቷ ክፍሎች ልዩነት ሳያደርግ በማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል አባላት ላይ የሚፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በመመርመር የሚያወጣቸዉ መግለጫዎችም በአገር ዉስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰመጉ ለሰብአዊ መብቶች መከበር ላደረገው በመርህ ላይ የተመሰረተ ተጋድሎ ምስክር ሆነው ይጠቀሣሉ።

ታዲያ ድርጅቱ ስለ አገራችን ዜጎች መብት እና ደህንነት ሲል ይህን ሁሉ ተግባር ሲያከናዉን ያለመስዋዕትነት አልነበረም።ይልቁንም ድርጅቱን የመሠረቱ፤ በተለያየ ጊዜ የመሩ፤ የድርጅቱ አባል የሆኑና ተቀጥረዉ ያገለገሉ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚወክሉ ኢትዮጵያዉያን ስለራሣቸዉ ሣይሆን ስለሌሎች መብት ስለተቆረቆሩና ስለታገሉ ብቻ ታስረዋል፤ በእስር ቤቶች ተሠቃይተዋል፤ ከሃገር ተሠደዋል እንዲሁ ዉድ ሕይወታቸዉን ሰዉተዋል። እንደ ማህበረሰባዊ ተቋም በሁሉም ማህበረሰባዊ ተቋማት ላይ ከተወሰደዉ የአፈና እርምጃ በተጨማሪ የድርጅታችንን ሕልዉና ለማክሰም የታቀዱ እና በተለይ በድርጅታችን ላይ ያነጣጠሩ መጠነ ሰፊ አስተዳደራዊ እና ሕገ-ወጥ የኃይል እርምጃዎች ሁሉ ተወስደዋል። ድርጅታችን በእነዚህ ሁሉ ፈተናዎች ዉስጥ ሆኖም ግን አንድም ጊዜ ቢሆን ለማንኛዉም የሰብአዊ መብት ተሚጋች ነኝ ለሚል አካል እጅግ መሠረታዊ ከሆነዉ የገለልተኛነት መርህ ፈቀቅ ብሎ አያዉቅም። ከለዉጡ በፊት የነበረዉ የመንግስት አስተዳደር ሰመጉ ለሰብአዊ መብቶች መከበር ያደርግ የነበረዉን ቁርጠኝነት የስጋት ምንጭ በማድረጉ በድርጅቱ ላይ ሲያካሂድ ከነበረዉ የስም ማጥፋት ዘመቻ ዉጪ የድርጅታችን ገለልተኛነት በማንኛዉም ሌላ አካል ጥያቄ ዉስጥ ወድቆ አያዉቅም።

ይሁን እንጂ እመቃዉ በፈጠረዉ ሥር የሰደደ የገንዘብ አቅምና የአሠራር ዉሱንነት፤በሕብረተሰቡ ዉስጥ በሰብአዊ መብት ጉዳይ ለመተባበር ከተፈጠረዉ ከፍተኛ ፍራቻ እና አንዳንድ የፌደራል እና የክልል መስተዳድር አካላት ራሣቸዉም ለድርጅታችን መረጃ ለመስጠት ያላቸዉ ፍላጎት አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተለይ በምናወጣቸዉ የሰብአዊ መብት ጥሰት ምርመራ መግለጫዎች ላይ ፈጽሞ ጉድለት ሊኖር አይችልም  የሚል ዕምነት የለንም። ይልቁንም በምናወጣቸዉ መግለጫዎች ሁሉ ይህንኑ የምንገልጽ ከመሆኑም በላይ ሊፈጠር የሚችለዉ ክፍተት ያልተገባ ትርጉም እንዳይሰጠዉ በማሰብም ሣይጣሩ የቀሩ ነገሮች ቢኖሩ በቀጣይ ሰፊና ዝርዝር ጥናት ለማድረግ እንዲቻል የሚመለከታዉ አካላት ሁሉ ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪ ማቅረባችን አልቀረም፡፡(በሪፖርቱ ገጽ  ተራ ቁጥር4-5 ሥር የተገለፀ)

ከዚህ በላይ ስለድርጅታችን አቋም፤ስለ ሥራዉ ዉጤት፤ስለተከፈለዉ መስዋዕትነት፤ ስለሚከተለዉ አሠራር እና መርህ መግለፃችን በሥራዉ ጉድለት ሲገኝበት ሊወቀስና ሊተች አይገባዉም ለማለት አይደለም። በተቃራኒዉ የተጠያቂነት ጉዳይ ድርጅታችን ሲያስተምራቸዉ ከነበሩት መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱ ሆኖ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ትችትም ሆነ ወቀሣ ገንቢ፤ በአግባቡ እና ለሚገባዉ አካል ብቻ ሲሆን ዉጤቱ ፍሬያማ ይሆናል።

ከዚህ አንፃር የሲዳማ ዞን ባሕል፤ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ፤ የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ባሕል፤ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን መምሪያ እና የሲዳማ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (አብዲን) ድርጅታችን በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን አስመልክቶ ሕዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም ያወጣዉን 146ኛ ልዩ መግለጫ ተከትሎ ያወጣችኋቸዉን የተቃውሞ መግለጫዎች ስንመለከት በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ፤ ሚዛናዊና ድርጅቱ የከፈለውን መስዋእትነት ግምት ውስጥ ያስገባ ነው ወይ የሚል ጥያቄ ማንሳታችን አልቀረም።

ከሁሉም በፊት ድርጅታችን በማናቸዉም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ጉዳይ የምርመራ ሥራን ሲያከናዉን ልምድ ያላቸዉን መርማሪዎች ጥሰት ወደተፈፀመበት አካባቢ በመላክ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ከማሰባሰብ በተጨማሪ ለጉዳዩ ቅርበት አላቸዉ ከሚላቸዉ መንግስታዊ አካላት ስለጉዳዩ መረጃ እንዲሰጠዉ በይፋ(በደብዳቤ)ጥያቄ ማቅረብ ሁሌም የሚከተለዉ አሠራር ነዉ፡፡በዚህም መሠረት ከሚያዝያ ወር 2010 ዓ.ም እስከ ሐምሌ 2010ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ዉስጥ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለማጣራት ባደረግነዉ ጥረት በመስክ በአካል በመገኘት ካደረግነዉ ማጣራት በተጨማሪ ሰኔ 27ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር አዋ/ስ/3497/10 ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ፤ለሲዳማ ዞን አስተዳደር ፤እና ለሐዋሣ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት እንዲሁም ሐምሌ 18 ቀን 2010ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር አዋ/ሰ/3508/10 በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ለሐዋሣ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ለሲዳማ ዞን ፖሊስ መምሪያ በአካባቢዉ ተፈጥሮ በነበረዉ ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸዉን ሰዎች ስም ዝርዝር እና የደረሰዉን የጉዳት አይነት፤የደረሰዉን የንብረት ዉድመት እና የዋጋ ተመን የሚገልጽ መረጃ ካላቸዉ እንዲልኩልን ጠይቀናል፡፡ ይሁን እንጂ የሲዳማ ዞን ፖሊስ መምሪያ ከላከልን ዉሱን መረጃ በቀር ሌሎቹ ተቋማት ለጥያቄያችን በአዎንታዊም ሆነ አሉታዊ መንገድ ምንም ዓይነት ምላሽ ያልሰጡን በመሆኑ በዚህ ሳንሰላች ነሐሴ 09 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር አዋ/ስ/3515/10 በተፃፈ ደብዳቤ ለሲዳማ ዞን አስተዳደር፤ለሐዋሣ ከተማ ፖሊስ መምሪያ፤ለሐዋሣ ከተማ አስተዳደር፤እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ለፍትህ እና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ በአካባቢዉ በደረሱ ግጭቶች የደረሰዉን የሰዉ ሕይወት መጥፋት፤የአካል ጉዳትና የንብረት ዉድመት የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ እንዲሰጠን እና መረጃዉን ለመስጠት የማይቻል ከሆነም ምክንያቱ ተገልጾ ምላሽ እንዲሰጠን በድጋሚ ጠይቀናል፡፡ ይሁን እንጂ ከፍ ብሎ እንደተገለጸዉ የሲዳማ ዞን ፖሊስ መምሪያ ከላከልን ዉስን መረጃ በቀር ከላይ የጠቀስናቸዉ የክልሉ እና የዞኑ ተቋማት ሁሉ ለሕጋዊ ተቋም መረጃ ለመስጠት ያላቸዉን ሕጋዊ ግዴታ በመጣስ ጭምር መረጃ ከልክለዉናል፡፡በመሆኑም በየትኛዉም ቦታ እና ጊዜ የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መመርመር እና ማጣራት የድርጅታን ዋነኛ ተልዕኮ ከመሆኑ አንፃር መንግስታዊ ተቋማት (የፌደራልም ሆነ የክልል) መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ባልሆኑ ጊዜ ሁሉ ተልዕኳችንን ሣንፈጽም መቅረት ስለሌለብን በዋነኛነት ጥሰቶቹ በተፈፀሙባቸዉ አካባቢዎች በመስክ ምርመራ ባገኘነዉ መረጃ ላይ በመመሥረት ማጣራቱን አድርገናል፡፡ ባለፉት 27 ዓመታትም ይህንኑ አሠራር ስንከተል ቆይተናል፡፡ እዚህ ላይ በመስክ ምርመራ በሚደረገዉ ማጣራት የሚገኘዉ መረጃ ሁሌም የተሟላ ላይሆን እንደሚችል መገመት አያቅትም፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ መንግስታዊ ተቋማት በእጃቸዉ ያለዉን መረጃ እንዲሰጡን የምንጠይቀዉም ለዚሁ ነበር፡፡

በመሆኑም በአካባቢዉ ተፈጥሮ ከነበረዉ ግጭት ጋር ተያይዞ በተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ጉዳዮች መረጃ እንዲሰጡን የተለያዩ የክልሉ እና የዞኑ አካላትን ጠይቀን በእጃቸው የሚገኙ መረጃዎችን ባልተሰጡን ሁኔታ ባወጣነዉ 146ኛ መግለጫ ላይ የታዩ ጉድለቶችን በማጉላት ስለ ኢትዮጵያ፤ ስለክልሉ እና ዞኑ ሕዝቦች እና ተወላጆች መብቶች ሲጮሕና ተቆጥሮ የማያልቅ ዋጋ ሲከፍል የነበረን ድርጅት ወገንተኛ፤ሆን ብሎ ጥላቻን ለመፍጠርና ሰላምን ለማደፍረስ የሚሰራ፤የሲዳማ ሕዝብ ብሎም መላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚኮራበትና በእጅጉ ለሚያከብረዉ የጨምበላላ በዓል ክብር እንደሌለዉ በማድረግ የቀረበብን ዉግዘትና ዉንጀላ ፈጽሞ ድርጅታችንንም ሆነ አባሎቻችንን የማይወክል እና በእጅጉም ያሣዘነን መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡
ከዚህ አጠቃላይ አስተያየታችን በተጨማሪ በመግለጫዎቻችሁ ላይ ላነሣችኋቸዉ አንዳንድ ትኩረት የሚያሻቸዉ ነጥቦች ላይ ያለንን ምላሽ ከዚህ እንደሚከተለዉ በዝርዝር እናቀርባለን፡፡

1. ድርጅታችን ያወጣዉ 146ኛ መግለጫ ሰመጉ ከተቋቋመበት መሠረታዊ ሐሣቦች ያፈነገጠና ተቋሙ ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር ገለልተኛነቱን ጥያቄ ዉስጥ የሚከት ነዉ የተባለዉን በተመለከተ ድርጅታችን በ1984 ዓ.ም ሲቋቋም ጀምሮ በወቅቱ መንግስት የዜጎችን የሰብዓዊ መብት ለማክበር እና ለማስከበር የነበረበትን ግልጽ ድክመት በመገንዘብ የሁሉንም ኢትዮጵያዉያኖች መብቶች ያለ ልዩነት እንዲከበሩ ለመወትወት የተቋቋመ የአገሪቱ ሕግም እንዲህ ዓይነቱ አቋም እንዲኖረዉ የሚያስገድደዉ ፤የድርጅቱ የመመሥረቻ እና የመተዳደሪያ ደንቦችም ይህንኑ በግልጽ የሚያመለክቱ፤ ላለፉት 27 ዓመታት ባደረግነዉ ተጋድሎ አንድም ጊዜ በዚህ መልክ ክስ ቀርቦበት የማያዉቅ፤ለመግለጫችን መነሻ በሆነዉ የሰብአዊ መብት ጥሰት ጉዳይም ወገንተኛ ለመሆን የሚያስችል አንዳችም ምክንያት የሌለ በመሆኑ እና ቀደም ባሉት ጊዜያት የነበሩትም ሆኑ አሁን ያለዉ አመራር እና ሠራተኞች እንደ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ስለ ገለልተኛነት መርህ በሚገባ የምንረዳና አጥብቀን የምናምን በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበብንን ወቀሣ የምንቀበለዉ አይሆንም

2. በ146ኛ መግለጫችን የተገለፀዉ ዉጤት ገለልተኛ አካልን ያላካተተ፤የግለሰቦችን አቤቱታ ብቻ ዋቢ ያደረገ፤የተጋነነ እና ተዓማኒነት የሚጎድለዉ ነዉ የተባለዉን በተመለከተ በምርመራ ወቅት ከሚገጥሙን መጠነ ሰፊ ተግዳሮቶች በመነሣት አንድም ጊዜ ቢሆን ያወጣነዉ መግለጫ የተሟላ እና እንከን የማይወጣለት ነዉ ብለን ገልፀን አናዉቅም፡፡ይልቁንም በምናወጣቸዉ መግለጫዎች ሁሉ በእያንዳንዱ ጉዳይ የቀሩ ነገሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት በቀጣይ ሰፊ እና ዝርዝር ጥናት ለማድረግ ቃል ስንገባና የሚመለከታቸዉ አካላት ሁሉ ለዚሁ ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪ ስናቀርብ ቆይተናል፡፡በዚሁ 146ኛ መግለጫችን ላይም _የምርመራ ስራዉ ዉሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች_ በሚለዉ ርዕስ ስር ይህንኑ ገልፀናል፡፡ አሁንም በዚሁ በመግለጫችን ላይ ታይተዋል የተባሉትን ጉድለቶች በማናቸዉም ጊዜ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ አካላት በሚደርሰን መረጃ መሠረት ለማሟላት ጥረት ከምናደርግ በቀር መግለጫችን በወቅቱ በአካባቢዉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ለመፈፀማቸዉ ለማረጋገጥ፤ፈፃሚዎችን ተጠያቂ ለማድረግ እና ተጎጂዎች እንዲካሱ ለመጠየቅ አቅም የሚያንሰዉ ነዉ ብለን አናምንም፡-

3. በጉጂ-ኦሮሞ እና በጌዴኦ ማህበረሰብ አባላት መካከል በተፈጠረዉ ግጭት የሟቾች ቁጥር እና ብሔር በሰንጠረዥ ተደግፎ የቀረበ ቢሆንም የሐዋሣን ግጭት በተመለከተ ግን በሠንጠረዥ 5 ላይ በዝርዝር አልተቀበረም የተባለዉን በተመለከተ እስካሁን በምንከተለዉ አሠራር ተጎጂዎችን በተመለከተ ከሚመለከተዉ አካል መረጃ ሲደርሰን በመረጃዉ የተገለፀዉ ጉዳት በርግጥም የደረሰ መሆኑን ማረጋገጣችን እንደተጠበቀ ሆኖ መረጃዉን ሣንጨምር ሣንቀንስ በመግለጫዎቻችን ስናካትት ቆይተናል፡፡በዚህም ጉዳይ በጉጂና በጌዴኦ ማህበረሰብ አባላት መካከል በተፈጠረዉ ግጭት የደረሰዉን ጉዳት አስመልክቶ መረጃዉን የላከልን የምዕራብ ጉጂ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት የተጎጂዎችን ብሔረሰብ ጭምር ገልፆ የላከልን ሲሆን፤በአንፃሩ በአዋሣ ከተማ ተፈጥሮ ከነበረዉ ግጭት ጋር ተያይዞ ስለደረሰዉ ጉዳት ከአደሬ ሆስፒታል ያገኘነዉ መረጃ ግን የተጎጂዎችን ብሔር የሚገልጽ አልነበረም፡፡ሐቁ ይህ ሲሆን እዚህ ላይ ግን ድርጅታችን ትኩረት የሚያደርገዉ ማንም ሰዉ ቢሆን ሕይወቱን ሊያጣ፤ አካሉ ሊጎል ወይም ሌላ ማንኛዉም የሰብዓዊ መብቱ ሊጣስ አይገባም የሚል ከመሆኑ አንፃር ወደ ፊት የተጎጂዎችን ብሔር በመግለጫዎቻችን ላይ ማካተትን አግባብነት የምናጤን ከሚሆን በቀር ሆን ተብሎ የአንዱን ተጎጂ የብሔር ማንነት በመግለጽ የሌላዉን ደግሞ ላለመግለጽ ተፈልጎ እንዳልሆነ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡ በሌላ በኩል ግን በሠንጠረዡ መግቢያ ሐሣብ ላይ *በሲዳማ ብሔር ተወላጆች በከተማዉና አካባቢዉ በሚኖሩ የወላይታ ተወላጆች በተፈፀመ ጥቃት* በሚል የተገለፀዉ ከሆስፒታሉ በተገኘዉ መረጃ ላይ ያልተመሠረተና አንድ ብሔር እንዳለ በሌላ ብሔር ላይ ጥፋት ፈጽሟል የሚል ትርጉም በሚያሰጥ መልክ የተገለፀ በመሆኑ ላልተገባ ትርጉም እንዳጋለጠ ድርጅታችን ይረዳል፡፡ ይልቁንም ድርጅታችን በመግለጫዉ የተካተቱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶችም ሆኑ ተያያዥ ችግሮች የትኛዉንም ብሔረሰብ በማይወክሉ በቡድን የተደራጁ ግለሰቦች የተፈፀሙ እንጂ በአንድ ብሔረሰብ የተፈፀሙ ናቸዉ ብሎ እንደማያምን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

4. በምርመራዉ የተሸፈኑት አካባቢዎች ሐዋሣ አካባቢ እንዲሁም ወላይታ ሶዶን የሚያካት ቢሆንም በወላይታ ሶዶ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከፎቅ ተወርዉረዉ ስለተገደሉ ሁለት የሲዳማ ተወላጅ ሴት ተማሪዎች፤ተደፍረዋል ስለተባሉ ስድስት ሴቶች እና ሽመና ገበያ ዉስጥ በተወረወረ ቦንብ ደርሷል ስለተባለዉ ጉዳት፤በወላይታ ፖሊሶች በጥይት ተደብድበዋል ስለተባሉ የሲዳማ ተወላጆች ጉዳይ በሪፖርታችን ያልተካተተዉ ደርጅታችን በአካባቢዉ ስለደረሰዉ የሰብአዊ ጥሰት ማጣራት ባደረገበት ወቅትም ሆነ ከዚያ በኋላ ስለ ጉዳዩ ከየትኛዉም አካል የደረሰዉ መረጃ ባለመኖሩ ነዉ፡፡ መረጃዉ በወቅቱ ደርሶን ቢሆን ዝርዝር ማጣራት የማናደርግበት እና ግኝታችንንም በሪፖርቱ የማናካትትበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም፡፡አሁንም ቢሆን በመግለጫዉ ላይ እንደጠየቅነዉ (ገጽ 9ተራ ቁጥር4.5) ስለ ጉዳዩ ከተጎጂ ቤተሰቦች እና ጉዳዩ ከሚመለከተዉ ማንኛዉም አካል መረጃ ከተላከልን ተጨማሪ ማጣራት የምናደርግበትና እንዳግባብነቱ በልዩ መግለጫ ወይም በመደበኛ መግለጫችን ላይ ይፋ እንደምናደርገዉ እንገልፃለን፡፡
5. ግጭቱ ከፍቼ ጨምበላላ በዓል ጋር መያያዙ አግባብ አይደለም የተባለዉን በተመለከተ በመግለጫችን የፍቼ ጨምበላላ በዓል የተጠቀሰዉ ግጭቱ የተፈጠረዉ በዓሉ በተከበረበት ወቅት (ጊዜ) መሆኑን ለመግለጽ እንጂ በምንም ዓይነት ሁኔታ የሲዳማ ማህበረሰብ ዓይነተኛ መገለጫ የሆነዉን እና አገራችንም በእጅጉ ከምትኮራባቸዉ እሴቶች አንዱ እና ዋነኛ የሆነዉን ባሕል በመናቅ ወይም የግጭት መነሻ አድርጎ በመዉሰድ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡እዚህም ላይ ድርጅታችን የየትኛዉንም ማህበረሰብ ባሕል ዝቅ አድርጎ ለማየት የሚከተለዉ የማይናወጽ መርህ የማይፈቅድለትና አንዳችም ምክንያት የሌለዉ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡
6. በሪፖርቱ ዉስጥ ቦታዎች ሲገለፁ በሲዳማ ዞን አስተዳደር ዉስጥ የሚገኘዉን ሎካ አባያ ወረዳን የወላይታ ዞን አስተዳደር ወረዳ እንደሆነ የተገለፀዉ ትክክለኛ እንዳልሆነ እና ሊታረም የሚገባዉ መሆኑን የተገነዘብን ሲሆን ነገር ግን ችግሩ በሥራ ሂደት የተፈጠረ እንጂ በሲዳማ ዞን ሥር ያለን አካባቢ ለወላይታ ዞን እሣልፎ ለመስጠት በማሰብ (ለማድረግም የማይቻለዉ) እንዳልሆነ ግንዛቤ እንዲወሰድልን እጠይቃለን፤
7. የሲዳማ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ሲብዴን) በክልሉ በተለያዩ የሐላፊነት ደረጃ ላይ የነበሩ ግለሰቦችን ስም በማንሣት ጥፋት ፈጽመዉ እያለ ያለአግባብ ወደ ፌደራል መንግስት መዛወራቸዉንና የቀድሞዉ ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማሪያም ደሣለኝም በክልሉ በሐላፊነት ላይ በነበሩ ጊዜ ነበራቸዉ የተባለዉን የተሣሣተ ፖሊሲ በማንሣት ድርጅታችን ያወጣዉ 146ኛ ሪፖርት እሣቸዉ ባደራጃቸዉ ካድሬዎች ተጽፎ በድርጅታችን ስም እንደወጣ የገለፀዉን በተመለከተ ምናልባት ስለ ድርጅታችን አንዳችም ዕዉቀት ካለመኖር የመነጨ እንደሆነ ለመገመት ቢቻልም በሌላ በኩል ግን አንድ በሕጋዊ መንገድ ተመዝግቦ በአገር ዉስጥ የሚንቀሳቀስ ተቋም ሌላ በሕግ መሠረት የተቋቋመን ድርጅት በዚህ ደረጃ ሲወነጅል ምን ያህል ሐላፊነት የጎደለዉ መሆኑን የሚያሣይ ነዉ፡፡ እስካሁን ከላይ በተከታታይ ስንገልፀዉ

እንደነበረዉ ድጅታችን በቀድሞዉ ጠ/ሚኒስትር ሐ/ማሪያም ደሣለኝ አገዛዝም ጭምር ፍዳዉን ሲያይ የነበረ እንጂ ከአቶ ኃ/ማሪያምም ሆነ ሌላ የመንግስት ባለሥልጣን ተፅዕኖ ውስጥ ወድቆ በትብብር የሚሰራበት አግባብ አልነበረም፤ ሊኖርም አይችልም፡፡ ወደፊትም ቢሆን ለየትኛዉም የፌደራልም ሆነ የክልል ባለሥልጣን ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ተጽዕኖ ሣይንበረከክ ነፃነቱን ጠብቆ የጀመረዉን የሠብአዊ መብት ትግል እንደሚቀጥል ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

**ማጠቃለያ፡-**

ደርጅታችን እስካሁን ሲያወጣቸዉ በነበሩ የሰብአዊ መብት ጥሰት ምርመራ ዉጤት መግለጫዎች ላይም ሆነ ሌሎች ሥራዎቹ ላይ ጉድለት ስለመኖሩ በሓላፊነት ስሜት ጥቆማ ሲደርሰንም ሆነ በራሣችን ስንረዳ ማስተካከያ ለማድረግ፤ ግልጽ ማድረግ በሚገባን ጉዳይ ላይ ደግሞ ተገቢዉን ማብራሪያ ለመስጠት ወደ ኋላ የምንልበት አንዳችም ምክንያት የለም፡፡ 146ኛ መግለጫችንን በተመለከተ ከተቋሞቻችሁ የቀረቡት ተቋዉሞዎች ግን በዚህ መልክ ያልቀረቡ ከመሆናቸዉም በላይ እጅግ በሚያሣዝን እና ኢ-ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ድርጅታችን ለሲዳማ ብሔር ፀር እንደሆነ አድርገዉ የሚያቀርቡ ናቸዉ፡፡ይህ በፍፁም ተገቢ አይደለም፡፡በመሆኑም በእኛም በኩል በመግለጫዉ ላይ ያስተዋልናቸዉን መሠረታዊ ያልሆኑ ጉድለቶች አግባብ ባለዉ መንገድ የምናርም መሆኑን እየገለጽን በእናተም በኩል ወደ ፊት ድርጅታችን ለሚያደርገዉ ማናቸዉም ሕጋዊ እንቅስቃሴ ትብብር በማድረግ ለተጀመረዉ የለዉጥ እንቅስቃሴ በጋራ ድጋፍ እንድናደርግ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

**የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)**

ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባል እና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው።